PSNP
Productive Safety Net Programme

# ምርጥ ተሞክሮ

## የአብክመ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ኮሚሽን



ለአደጋ የማይበገርና የምግብ ዋስትናዉ የተረጋገጠ ማህበረሰብ እንፈጥራለን!



በህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት

የተዘጋጀ ቡክሌት

ግንቦት/2017 ዓ/ም

## የኮሚሽኑ ራዕይ እና ተልዕኮ

## ራዕይ

- **የአማራ ክልል ህዝብ** አደጋን የመከላከልና የመቋቋም አቅሙ ጎልብቶ፣ የምግብ ዋስትናው ተረጋግጦ፣ የዳበረ ልማት ተጠቃሚ ሆኖ ማየት!

## ተልዕኮ

- በክልሉ ውስጥ የሚከሰቱ የምግብ ዋስትና እጦት ችግሮችንና መሠረታዊ መንስኤዎችን በማጥናት፣ ህብረተሰቡን በልዩ ልዩ የልማት ኘሮጀክቶችና ኘሮግራሞች በማሳተፍና የተለያዩ የልማት አጋሮችን በማስተባበር አደጋን መከላከል፣ የምግብ ዋስትናን በዘላቂነት ማረጋገጥና ድህነትን መቀነስ!

## የኮሚሽኑ ዓላማዎች

- በአስከፊዉ የድህነት ችግርና ስር በሰደደ የምግብ ዋስትና መጣጣት ሳቢያ በሚጠቁ የክልሉ አካባቢዎች የሚኖረዉና በቋሚነት ለችግሮቹ የተጋለጠዉ ሕዝብድህነቱ በዘላቂነት እዲወገድለትና የምግብ ዋስትናዉ እዲረጋገጥለት ዘላቂ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ለማምጣትየሚካሄዱ ጥረቶችን ማስተባበርና መደገፍ፣
- የከፋ የድህነት ችግርና የምግብ ዋስትና መጣጣት ጎልቶ በሚታይባቸዉ ስፍራዎች የሚከሰቱ አደጋዎችን መሰረታዊ መንስኤዎች በማጥናትና የተፈጥሮ አካባቢን መልሶ ለማቋቋም የሚደረጉ ሁለገብ ጥረቶችን ማገዝ፣
- ለአደጋ ሰለባዎች አስፈላጊዉን የምግብና ሌሎች መሰረታዊ የኑሮ ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያስፈልገዉ እርዳታ በወቅቱ መድረሱን ማረጋገጥ፣ ሕብረተሰቡን ከጥገኝነትና ከጠባቂነት መንፈስ ለማላቀቅ ይቻል ዘንድ አደጋ ሊያደርስ የሚችለዉን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችል አቅምን አስቀድሞ ማጎልበት::

PSNP
Productive Safety Net Programme

## ሎኮ የመስኖ ካናል (ጎበራ ክላስተር)



ሎኮ የመስኖ ካናል

ሎኮ የመስኖ ካናል የሚገኘዉ በአርጎባ ወረዳ ቀበሌ 07 በጎበራ ክላስተር ዉስጥ ሲሆን የተገነባዉ በ2007 ዓ.ም በገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የካፒታል በጀት ነዉ።





የመስኖ ፕሮጀክቱ ከ354 ሄክታር መሬት በላይ የማልማት አቅም ሲኖረዉ ከ400 በላይ የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ይገኙበታል።



እየለማ ያለ የመስኖ ልማት

## ድህነትን በጥረታቸዉ የተሻገሩት አርሶ አደር



አርሶ አደር ሙሀመድ አሊ

በጥረታቸዉ በስራ ወዳድነታቸዉ ከተረጅነት የወጡት አርሶ አደር ሙሀመድ አሊ የሚኖሩት በአርጎባ ልዩ ወረዳ በአሮዬ ቀበሌ ሲሆን ከዚህ በፊት የሴፍቲኔት ተጠቃሚ የነበሩ ናቸዉ። አርሶ አደር ሙሀመድ ዘጠኝ ቤተሰብ ያስተዳድራሉ።

ወደ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ከመግባታቸዉ በፊት ምንም ዓይነት ሃብት ያልነበራቸዉና በችግር ዉስጥ የሚኖሩ ነበሩ።



አርሶ አደር ሙሀመድ አሊ በእርሻ ስራ ላይ

ወደ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ከገቡ በኂላ በሚደረግላቸዉ ድጋፍ በኑሯቸዉ መሻሻል እያሱና እየተለወጡ እንደመጡ ይናገራሉ፡፡

አርሶ አደር ሙሀመድ በፕሮግራሙ ካፒታል በጀት በ2007 ዓ/ም የተሰራ የመስኖ ካናልን በመጠቀም ባላቸዉ መሬት ላይ የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ከዕለት ፍጆታ አልፈዉ ቋሚ ሃብት በማፍራት በ2013 ዓ/ም አካባቢ ከፕሮግራሙ ራሳቸዉን ችለዉ ተመርቀዉ ወጠዋል፡፡




በአሁኑ ሰዓት ሁለት የእርሻ በሬዎች፣ ሁለት ላሞች፣ በርካታ ፍዬሎች አሏቸዉ፡፡ ከሁለት ቀን በላይ የሚያዉል መሬት አላቸዉ፡፡

በዚህም ሎኮ የመስኖ ካናልን በመጠቀም በዓመት ሶስት ጊዜ የተለያዩ ሰብሎችን በማምረትና ፍራፍሬችን በማልማት ተለዉጠዋል፡፡

# ደለመሌ የተፋሰስ ልማት




ደለመሌ የተፋሰስ ልማት የሚገኘዉ በአርጎባ ወረዳ 01 ቀበሌ ሲሆን በሴፍቲኔት ፕሮግራም በማህበረሰብ ልማት የለማ ነዉ፡፡

በተፋሰስ ልማቱ ከ1ሽህ 89 በላይ ወጣቶች በማህበር ተደራጅተዉ አትክልትና ፍራፍሬ እያለሙበት ይገኛል፡፡ ተጠቃሚዎችም የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችና ከሴፍቲኔት ዉጭ ያሉ የአካባቢዉ ወጣቶች ናቸዉ፡፡

ሌላዉ የተፋሰሱ ትሩፋት ከ23 በላይ ወጣቶችና ተጠቃሚዎች በማህበር ተደራጅተዉ በንብ ማነብ ስራ ተሰማርተዉ ሃብት ፈጠራ ላይ ይገኛሉ።

በዚህም የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችም ሆኑ የአካባቢዉ ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶች ከዕለት ፍጆታ ያለፈ ጥሪት እያፈሩበት ያለና ከኑሮ መሰረት ማሻሻያ ስራዎች ጋር ተሳስሮ እየተሰራበት የሚገኝ የፍራፍሬዎች አምባ ነዉ።



ደለመሌ የፍራፍሬዎች አምባ

# ከተረጅነት ለመዉጣት እየተጋች ያለች ጠንካራ ሴት



ወ/ሮ ዘሃራ ዳዉድ

ወ/ሮ ዘሃራ ዳዉድ ትባላለች። የምትኖረዉ በአርጎባ ብሔረሰብ ልዩ ወረዳ መዲና ከተማ 01 ቀበሌ ሲሆን ሰባት ቤተሰብ ያስተዳድራሉ። በስድስት ቤተሰብ በሴፍቲኔት ታቅፈዉ ድጋፍ እያገኘች ነዉ።

ወ/ሮ ዘሃራ ዳዉድ ወደ ሴፍቲኔት ከመግባቷ በፊት ምንም ዓይነት ሃብት ያልነበራት ወደ ጅቡቲ እየሄደች የጉልበት ስራ እየሰራች የምትኖር ነበረች።

በደለመሌ ተፋሰስ ዉስጥ ከሌሎች መሰል ጓደኞቿ ጋር በማህበር ተደራጅታ በንብ ማነብ እና ፍራፍሬ ልማት ተሰማርታ እያለማች ትገኛለች።

ወ/ሮ ዘሃራ ታታሪ የሆነችና ከተረጅነት ለመዉጣት እየተጋች ያለች ጠንካራ ሴት ነች፡፡

በቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ዘርፍ በተመቻቸ 25 ሽህ ብር ብድር ወስዳ ከፍራፍሬ ልማቱና ከንብ ማነብ ስራዉ በተጨማሪ ፍዬል እያረባች ኑሮዋን ትደጉማለች፣ ጥሪትም እየገነባች ያለች ተጠቃሚ ናት፡



:

ወ/ሮ ዘሃራ ከማንጎ ልማቱ በአንዴ ከ35 ሽህ ብር በላይ እንዳገኘች፣ ከንብ ማነቡ ደግሞ እንደ ማህበር ወደ 800ሽህ ብር የሚጠጋ ገቢ እንዳገኘች ታስረዳለች፡፡



የዘሃራ እና ጓደኞቿ የንብ ቀፎዎች

አሁን በተጨባጭ ወ/ሮ ዘሃራ ብድሯን ሙሉ ለሙሉ መልሳ ከ30 በላይ ፍየሎች፣ሁለት በሬዎች አሏት፡፡ ማሽላና ማሾ ታመርታለች፣ ልጆቿን ጥሩ ትመግባለች፣ የሚያስፈልጋቸዉን ሁሉ እያሟላች በማስተማር ላይ ትገኛለች፡፡

በዚህ ዓመት ራሳቸዉን ችለዉ ከሚመረቁ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ዉስጥ አንዷ ናት፡፡

# በፍዬል እርባታ የተለወጡ



አቶ አሊ ሰይድ

አቶ አሊ ሰይድ ይባላሉ፡- ነዋሪነታቸዉ በመዲና ከተማ ሰንቀሌ ቀበሌ ሲሆን ስምንት ቤተሰብ ያስተዳድራሉ፡፡

አቶ አሊ ሰይድ ከ1993 ጀምሮ ወደ ጅቡቲ ተሰደዉ ሢኖሩ የነበሩ ናቸዉ፡፡ የስደት ኑሮ አልሆን ሲላቸዉ ወደ ሃገራቸዉ ተመልሰዉ በ2006 ዓ/ም ወደ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተመልምለዉ ገብተዋል፡፡

በፕሮግራሙ ከታቀፉ በኋላ በኑሮ መሰረት ማሻሻያ ዘርፍ በተመቻቸላቸዉ ብድር 10 ግልገል ፍየሎችን ገዝተዉ ወደ እርባታ ገቡ፡፡

በፍዬል እርባታዉም ዉጤታማ እየሆኑና ሃብት እያፈሩ መጡ፡፡ ከፕሮግራሙም ራሳቸዉን ችለዉ በ2012 ዓ/ም አካባቢ ተመርቀዉ ወጠዋል፡፡

አቶ አሊ ታታሪና ጀግና የሆኑ፣ በጥረታቸዉ ድህነትን የተሻገሩ፣ የሰርቶ መለወጥ ማሳያ ጠንካራ አርሶ አደር ናቸዉ፡፡ እነዚያ አስር ግልገል ፍዬሎች በ2011 ዓ/ም አካባቢ ከ200 በላይ ደርሰዉ እንደነበር በአንደበታቸዉ ይናገራሉ፡፡




የአቶ አሊ ሰይድ ፍዬል እርባታ

በፍየል ሽያጭ ብድራቸዉን ሙሉ ለሙሉ መልሰዉ ከጎጆ ቤት ወደ ቆርቆሮ ቤት በመሸጋገር ከ110 ቅጠል በላይ 7 ክፍል ያለዉ ቆርቆሮ ቤት ሰርተዋል፡፡

ከ120 በላይ ፍዬሎች፣ ሁለት በሬዎች፣ ላሞችን ገዝተዋል፣ ባላቸዉ መሬት ላይና ከሌሎች ሰዎች መሬቶችን በመከራየት ማሾና ማሽላ እያመረቱ የምግብ እህላቸዉን ያሟላሉ፡፡

አቶ አሊ ከስደት ተመልሰዉና ከምንም ተነስተዉ ዛሬ ላይ በኑሯቸዉ ተለዉጠዋል፣ ቋሚ ሃብቶችንም ፈጥረዉ ለሌሎች እየተረፉ ይገኛል፡፡ በዚህም እርዳታን ወደ ስራ በመቀየር ጠንክረዉ በመስራታቸዉ ድህነትን አሸንፈዋል፡፡

ወደፊት ከፍዬል እርባታ ባለፈ የእርሻ መኪና እና ለወረዳዉ የሚጠቅም መንገድ የሚጠርግ እስካቫተር የመግዛት ዕቅድ እንዳላቸዉ ይናገራሉ፡፡





የአቶ አሊ ሰይድ በሬዎች

# “አብቾ” ሴፍትኔት የቀየራት ክላስተር



አብቾ በደቡብ ወሎ ዞን ቃሉ ወረዳ 019 ቀበሌ ዉስጥ የምትገኝ ክላስተር ናት፡፡ በ019 ቀበሌ ዉስጥ በአጠቃላይ ከ232 በላይ የሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ይገኛሉ፡፡

በአብቾ ክላስተር ዉስጥ በ2011 ዓ/ም በሴፍቲኔት ካፒታል በጀት የተገነባ ጎቱ የተሰኘ አነስተኛ የመስኖ ግድብ ይገኛል፡፡ ግድቡ የተገነባዉ 32 ሄክታር መሬት እንዲያለማ ታስቦ የተሰራ ነዉ፡፡

ቀበሌዋ ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት የዉሃ አማራጭ ያልነበራትና የመስኖ ልማትም የማይታወቅባት ደረቅ አከባቢ ነበረች፡፡

አሁን ግን ጎቱ የመስኖ ግድብን በመጠቀም ከ112 በላይ የሚሆኑ አርሶ አደሮች በልማት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ዉስጥ ደግሞ ወደ 38 የሚሆኑት የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ናቸዉ፡፡




በዚች ክላስተር የሚገኙ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችም ሆነ የአካባቢዉ አርሶ አደሮች ያገኙትን የዉሃ አማራጭ በመጠቀም ባላቸዉ መሬት ላይ የተለያዩ ልማቶችን በማልማት ከተረጅነት ለመዉጣትና ሃብት ለመፍጠር እየተጉ ይገኛል፡፡

የሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ ለሆኑ አርሶ አደሮች ጥሪት ገንብተዉ ከፕሮግራሙ እንዲመረቁ የዉሃ መሳቢያ ሞተር ፓምፕ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡

ተጠቃሚዎች በምግብ ራሳቸዉን ለመቻል ባላቸዉ ዉስን መሬት ላይ የጓሮ አትክልቶች፡- ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ቃሪያ....፣ ቋሚ ፍራፍሬዎች፡- ማንጎ፣ ቡና፣ ሙዝ፣.....) እያለሙ ይገኛል፡፡




ፕሮግራሙ በሰራዉ የመስኖ ፕሮጀክት የዕለት ጉርስ የሌላቸዉ አሁን ላይ በዓመት ሁለቴና ሶስቴ በማልማት ሃብት እያፈሩ ይገኛል፡፡ ከምንም ተነስተዉ ቆርቆሮ ቤት ሰርተዋል፣ በሬዎችን፣ ፍዬሎችንና ላሞችን ገዝተዋል፣ ልጆቻቸዉን ያስተምራሉ፣ ቁጠባም ጀምረዋል፡፡



በዚች ክላስተር የሚገኙ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ዘጠኝ ጊዜ የሚለቀም ቬግሮ የተሰኘ የቃሪያ ዝርያ ያለማሉ፣ በጣም ምርታማና ዉጤታማ ነዉ።

አንድ አርሶ-አደር ከ2 መቶ ካሬ መሬት ላይ ከአንድ መቶ ሽህ ብር በላይ ገቢ አግኝቶበታል በዚህ የቃሪያ ዝርያ።




በዚህ ዓመት በፕሮግራሙ በተደረገላቸዉ ድጋፍ በመነሳት ሃብት የፈጠሩ አራት የሚሆኑ የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች በራሳቸዉ ተነሳሽነትና ፈቀድ ተረጅነት በቃን በማለት ከፕሮግራሙ ወጠዋል።

አሁን ላይ አብቾ ቀበሌ የሴፍቲኔት ፕሮግራም አበርክቶና አሻራ በግልጽ የሚታይባት፣ በመስኖ ልማትና በፍራፍሬ ልማት የምትታወቅ ሞዴል አካባቢ ሆናለች።

## ታታሪዋ አሚናት ሰይድ



ታታሪዋ አሚናት ሰይድ

ወ/ሮ አሚናት ሰይድ ሀሰን የምትኖረዉ በቃሉ ወረዳ አብቾ ቀበሌ ሲሆን አራት ቤተሰብ የምታስተዳድር የሴፍቲኔት ተጠቃሚ ናት።

በ2013 ዓ/ም ነዉ ወደ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የታቀፈችዉ። ወ/ሮ አሚናት ምንም ያልነበራት በፕሮግራሙ በሚደረግላት ድጋፍ ልጆቿን ብቻዋን የምታሳድግ ነበረች።

በ2013 በሴፍቲኔት ፕሮግራም ካፒታል በጀት የተሰራዉን ጉቱ የመስኖ ግድብ በመጠቀም ባላት መሬት ላይ በማልማት ተጠቃሚ እየሆነች ትገኛለች፡፡

በተደረገላት የዉሃ መሳቢያ ሞተር ፓምፕ በመታገዝ ቋሚ ፍራፍሬዎችን፣ የጓሮ አትክልቶችን በዓመት እስከ ሶስት ጊዜ በማልማት በኑሮዋ እየተለወጠችና ሃብት እያፈራች እንደሆነ ተናግራለች፡፡



ታታሪዋ አሚናት ሰይድ በስራ ላይ

ከማንጎ ብቻ በአንድ ጊዜ ወደ 40,000 ብር ታገኛለች፣ ከጓሮ አትክልቶችም እንዲሁ ገቢ እያገኘች ልጆቿንም በማስተማር ላይ ትገኛለች፡፡

አሚናት ለአካባቢዉ ማህበረሰብ ሞደል የሆነች ታታሪ አርሶ አደር ናት፡፡

## ተረጅነታቸው ምቾት ያልሰጣቸው ታታሪው አርሶ አደር



አርሶ አደር ሰኢድ ኢብራሂም

በደቡብ ወሎ ዞን ቃሉ ወረዳ አብቾ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሰኢድ ኢብራሂም ምንም አይነት ገቢ የሌላቸውና የቀን ስራ እየሰሩ በድህነት የሚኖሩ ነበሩ፡፡

በ2001 አካባቢ ወደ ሴፍቲኔት ፕሮግራም እንዲገቡ ተደርገው ሲረዱ ኑረዋል፡፡ አቶ ሰኢድ ኢብራሂም ባለ ትዳርና የስድስት ቤተሰብ አባወራ ናቸው፡፡ በሴፍቲኔት ፕሮግራም በአራት ቤተሰብ ድጋፍ ይወስዱ ነበር፡፡

ይህ ተረጅነታቸው ምቾት ያልሰጣቸው ታታሪው አርሶ አደር አቶ ሰኢድ በ2011 ዓ/ም በአብቾ ቀበሌ በፕሮግራሙ የካፒታል በጀት በተሰራ አነስተኛ የውሃ ግድብን በመጠቀም ባላቸው መሬት ላይ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ማልማት ጀመሩ፡፡

በተደረገላቸው የውሃ መሳቢያ ሞተር ፓምፕ በመታገዝ ጠንክረው በመስራታቸው ከዕለት ፍጆታ ባለፈ ጥሪት እያፈሩ መጡ:: ልጆቻቸውንም የሚያስፈልጋቸውን እያሟሉ በማስተማር፣ በኑሯቸውም እየተለወጡ እንደመጡ ይናገራሉ::

ያለውን የውሃ አማራጭ በመጠቀም ባላቸው ሁለት ጥማድ መሬት ላይ ጤፍ፣ ማሽላ፣ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን እና ቋሚ ፍራፍሬዎችን በማልማት ገቢያቸው በማደጉና ሃብት በማፍራታቸው በዚህ ዓመት በራሳቸው ፈቃድ ተረጅነት በቃኝ በማለት ከሴፍቲኔት ፕሮግራም እንደወጡ በአንደበታቸው ነግረውናል::



አርሶ አደር ሰኢድ ኢብራሂም በልማት ስራ ላይ

አቶ ሰኢድ ኢብራሂም ለሌሎች ትምህርት የሚሰጡና ተሞክሯቸው ሊሰፉ የሚገባ ታታሪ ሰራተኛ ናቸው::

አሁን ላይ ከምንም ተነስተው ሰፊ የልማት ቦታ አላቸው፣ ለመቁጠር የሚያዳግት ቋሚ ፍራፍሬ፣ የጓሮ አትክልቶች፣ የምግብ እህላቸውን የሚችሉበት ጤፍና ማሽላ ያመርታሉ፣ ሁለት በሬዎች፣ ከ3 በላይ ፍየሎች አላቸው: ቁጠባም ጀምረዋል::



አርሶ አደር ሰኢድ ኢብራሂም በሬዎች እና ፍዬሎች

ሰርቶ መለወጥና ከተረጅነት መውጣት እየተቻለ እርዳታን መጠበቅ ከሀይማኖትም ሆነ ከባህል አንጻር የማይደገፍ በመሆኑ ሌሎች ከእርሳቸው መማር አለባቸዉ ይላሉ::

# በሽሎ አንድ የመስኖ ፕሮጀክት ግንባታ



በሽሎ አንድ አነስተኛ የመስኖ ፕሮጀክት በደቡብ ወሎ ዞን ቃሉ ወረዳ ቦሰና/09 ቀበሌ ይገኛል፡፡ በገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ካፒታል በጀት በዘጠኝ ሚሊዮን ብር የዌርና ካናል እየተካሄደ ነዉ፡፡




ፕሮጀክቱ 25 ሄክታር መሬት ያለማል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን ወደ ሰማኒያ ሁለት አርሶ አደሮችን ጠጠቃሚ ያደርጋል ተብሎ እየጠሰራ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ዉስት 12 የሚሆኑት የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ናቸዉ፡፡

# ጨርቆቲ የመስኖ ካናል

በ2017 በጀት ዓመት በገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ካፒታል በጀት በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ባቲ ወረዳ በጨርቆቲ ቀበሌ የተገነባ ነዉ፡፡



የመስኖ ፕሮጀክቱ 1 ሽህ ኪሎ ሜትር ርዝመት አለዉ፡፡ 10 በ 8 ስፋት ያላቸዉ 3 ጊዜያዊ የዉሃ ማጠራቀሚያ ሲኖረዉ እያንዳንዳቸዉ 160 ኪዩብ ዉሃ የመያዝ አቅም አላቸዉ፡፡

7.6 ሚሊዮን ብር በፕሮግራሙ በጀት ተይዞለት የተሰራ ነዉ። ከ37 ሄክታር መሬት በላይ ያለማል ተብሎ ይጠበቃል።



ጊዜያዊ የዉሃ ማጠራቀሚያ(Night Storage)

አርባ አራት የሚሆኑ የአካባቢዉ አርሶ አደሮችን በመስኖ ልማት ተጠቃሚ የሚያደርግ ሲሆን ከእነዚህ ዉስጥ ወደ 12 የሚሆኑት የሴፍቲኔት ተጠቃሚ የሆኑ አርሶ አደሮች ናቸዉ።



ጊዜያዊ የዉሃ ማጠራቀሚያ(Night Storage)

## በፍራፍሬ ልማት ዉጤታማ የሆኑት ታታሪዉ አርሶ አደር



አርሶ አደር አብዱ አበጋር

አርሶ አደር አብዱ አበጋር በባቲ ወረዳ በጨርቆቲ ቀበሌ መንጦር ጎጥ ኗሪ ሲሆኑ ሰባት ቤተሰብ አላቸዉ። ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት ሃብት ያልነበራቸው በመሆኑ የደሃ ደሃ ተብለው በአምስት ቤተሰብ በሴፍቲኔት የሚረዱ ነበሩ።

በስራና በልማት ከተረጅነት ወጥተው ለብዙ የአካባቢው አርሶ አደሮችና ተጠቃሚዎች ተምሳሌት የሆኑት እኒህ ጀግና አርሶ አደር አብዱ አበጋር ወደ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ከገቡ በኋላ በተደረግላቸው ድጋፍ የፓፓያ ፍራፍሬ ለማልማት ሲሞክሩ

PSNP
Productive Safety Net Programme

በቅርብ ውሃ ስላልነበረ በቅል በትክሻቸው እየተሸከሙ በሗላም አህያ ገዝተው አምጥተው እያጠጡ ነበር ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩት።


አርሶ አደር አብዱ የፍራፍሬ ልማት

እኒህ ጀግና አርሶ አደር የተሞክሮ መቅሰሚያና የልምድ ልውውጥ ማዕከል በመሆን ሊያገለግሉ የሚችሉት፣ እርዳታን ወደ ልማት በመቀየርና ሰርቶ መለወጥ እንደሚቻል ያሳዩት የቋሚ ፍራፍሬዎችና የጓሮ አትክልቶች ጫካ የፈጠሩት በጥረታቸው ህየወታቸዉን ቀይረዋል።

በሂደት በፕሮግራሙ የውሃ ማቆርና ጀኔረተር ድጋፍ አግኝተው ከዕለት ጉርስ አልፈው የሚታይ ለውጥ በማምጣታቸውና ሃብት ስላፈሩ ከፕሮግራሙ ወጠዋል።

በ2016 በጀት ዓመት የጨቆርቲ ቀበሌ አርሶ አደሮችንና የሴፍቲኔት ተረጅዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ፣ በመስኖ ልማት ተሰማርተዉ ሃብት እንዲያፈሩና ከተረጅነት እንዲላቀቁ ለማስቻል በገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ካፒታል በጀት ተገንብቶ በተጠናቀቀው 6 መቶ ሜትር ርዝመት ያለው የመስኖ ካናልን ተጠቅመው በከፍተኛ ልማት ውስጥ ይገኛሉ።

በአሁኑ በቁጥር ለመግለጽ የሚከብድ ማንጎ፣ ፓፓያ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ለውዝ፣ ሸንኩርት፣ ቲማቲም፣ቃሪያ፣ ድንች፣ አርቲና ሌሎች ነገሮችን በማልማት ድህነትን በመሻገር ታሪክ አድርገውታል።


አርሶ አደር አብዱ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት

ከካናሉ ተጠቅመው የሚተርፈውን ውሃ በሶስት ጉድጓዶች በማቆር ከተራቸው ባለፈ ለሚያለሙት አትክልቶች፣ ፍራፍሬዎች፣ እና ለሌሎች አዝርዕት ይጠቀማሉ።

ይህን የሚያደርጉትም በግላቸው ገዝተው በርካታ ኤች ዲ ፒ ቱቦዎችን በሰፊ መሬታቸው ላይ በተለያዩ አቅጣጫ በመዘርጋትና ወደ ልማታቸው እንዲደርስ በማድረግ ነው።

ተረጅነትን በመጸየፍ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በመስራታቸው የራሳቸውንም ሆነ የቤተሰባቸውን ኑሮ በእጅጉ አሻሽለዋል፡፡




የሚቆጠር ሃብት አፍርተዋል፡፡ ለዚህ ለመድረሳቸው እንደምክንያት የሚጠቅሱት ደግሞ የገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ነው ይላሉ፡፡

ከአትክልትና ፍራፍሬ እና ከሌሎች ልማቶች ባለፈ በጎችንና ወይፈኖችን በመግዛት ለሌሎች ወገኖች ለእኩል ተጠቃሚነት ለርቢ ይሰጣሉ፡፡ በዚህም ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች እየተረፉ ይገኛሉ፡፡

ከሴፍቲኔት ተጠቃሚነት ተሸጋግረው በጥረታቸውና በትጋታቸው ድህነትን የተሻገሩትና ቋሚ ሃብት ያፈሩት አርሶ አደር አብዱ የወደፊት ህልማቸው የሚያመርቱትን አትክልትና ፍራፍሬ እዛው ከሚያለሙበት ቦታ ቀጥታ በመኪና ወደ ገበያ ለማቅረብ ዕቅድ አላቸዉ፡፡

# ሀጦ የመስኖ ፕሮጀክት



በኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን ባቲ ወረዳ ሀጦ ቀበሌ በ2017 በጀት ዓመት በሴፍቲኔት ካፒታል በጀት 7 መቶ ሜትር ርዝመት ያለው የመስኖ ካናል ተገንብቶ ተጠናቋል፡፡

የመስኖ ፕሮጀክቱ ከ4.1 ሚሊዮን ብር በላይ ተመድቦለት የተሰራ ፕሮጀክት ነው፡፡ ከ37 ሄክታር መሬት በላይ የሚያለማ ሲሆን 43 አባወራዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡

PSNP
Productive Safety Net Programme

በዚህ የመስኖ ካናል ተጠቃሚ ከሆኑ አርሶ አደሮች ዉስጥ ወደ አስራ ሁለት የሚሆኑት የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ናቸዉ፡፡

የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ባላቸዉ መሬት ላይ በዓመት ሁለቴና ሶስት ጊዜ በማምረት በምግብ ራሳቸዉን እንዲችሉና ከተረጅነት እንዲወጡ ታስቦ የተሰራ ነዉ፡፡





በፕሮጀክቱ ተፋሰስ ዉስጥ የሚገኙ ከሴፍቲኔት ዉጭ ለሆኑ አርሶ አደሮችም የዉሃ አማራጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በመስኖ ካናሉ አረሶ አደሮች የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎችን፣ የጓሮ አትክልቶችን፣ ለውዝና የመሳሰሉ ሰብሎችን እያለሙበት ይገኛል፡፡

# ጠንክረዉ በመስራታቸዉ ከሴፍቲኔት የወጡት አርሶ አደር

አቶ አብዱ አህመድ ይባላሉ፡፡ የሚኖሩት በሀጠ 16 ቀበሌ ሲሆን ከ1998-2013 ዓ/ም በ4 ቤተሰብ የሴፍቲኔት ተጠቃሚ የነበሩ ናቸዉ፡፡

በፕሮግራሙ በተደረገላቸዉ ድጋፍና ክትትል ከዕለት ጉርስ ያለፈ ጥሪት ስላፈሩ በ2013 ዓ/ም አካባቢ ሃብት ፈጥረዉ ከፕሮግራሙ ተመርቀዉ ወጠዋል፡፡


አርሶ አደር አብዱ አህመድ

አቶ አብዱ በአሁኑ ሰዓት ዘጠኝ ቤተሰብ የሚያስተዳድሩ ሲሆን በሴፍቲኔት ፕሮግራም የተሰራ ሀጦ የመስኖ ካናልን በመጠቀም ለዉዝ፣ ማንጎ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ቲማቲም ቃሪያና የመሳሰሉትን እያለሙ ተጠቃሚ ሁነዋል፡፡



የአርሶ አደር አብዱ አህመድ ልማት

አቶ አብዱ ጠንክረዉ በመስራታቸዉ ከተረጅነት በመዉጣት በኑሯቸዉ ተለዉጠዋል፣ ራሳቸዉንና ቤተሰባቸዉን እያስተዳደሩ ይገኛል፡፡

# ከግብርና ዉጭ ገቢ ማስገኛ ዘዴ የተሰማሩ ዉጤታማ ተጠቃሚዎች



ወ/ሮ ዘይነባ ሙሀመድ

ወ/ሮ ዘይነባ ሙሀመድ ይባላሉ የሚኖሩት በባቲ ወረዳ በሃጦ 06 ቀበሌ ነዉ፡፡ አራት ቤተሰብ ያስተዳድራሉ፡፡

የገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በኑሮ መሰረት ማሻሻያ ዘርፍ የብድር ተጠቃሚ ናቸዉ፡፡ ተጠቃሚዎች በመረጡት፣ አዋጭና ተስማሚ በሆኑ ተግባራት ተሰማርተዉ ሃብት እንዲፈጥሩ ለማድረግ ድጋፍና ክትትል እየተደረገ ገኛል፡፡

PSNP
Productive Safety Net Programme

ወ/ሮ ዘይነባ ሙሀመድ 35 ሺህ ብር ለሶስት ዓመታት ከወለድ ነጻ በሆነ መንገድ ወስደዉ ከግብርና ዉጪ ገቢ ማስገኛ ዘዴ በሸቀጣሸቀጥ ንግድ የተሰማሩ ናቸዉ፡፡

ወ/ሮ ዘይነባ ከምንም ተነስተዉ ባገኙት ብድር በመረጡት ዘርፍ ተሰማርተዉ በስራቸዉ ዉጤታማ ሆነዋል፡፡ የአንድ ዓመት የብድር ዕዳቸዉን መልሰዋል፡፡ በኑሯቸዉም መሻሻል አሳይተዋል፡፡

አራት ክፍል ቤት ሰርተዋል፣ ከሸቀጣሸቀጡ ንግድ ጎን ለጎን አትክልትና ፍራፍሬ ያለማሉ፡፡ መሬት እየተከራዩ በማሳረስ የምግብ እህላቸዉን ይችላሉ፡፡

በሴፍቲኔት ፕሮግራም አማካኝነት ባገኙት ብድር በገቢ ማስገኛ ስራ በመሰማራት ከተረጅነት ለመዉጣት ጠንክረዉ እየሰሩ ይገኛል፡፡

ወደፊት ያለባቸዉን እዳ ሙሉ ለሙሉ ከፍለዉ የንግድ ስራቸዉን ከዚህ በተሻለ ለማስፋፋት እዳሰቡ ይናገራሉ፡፡



አቶ እንድሪስ ኢብራሂም

አቶ እንድሪስ ኢብራሂም የሀጦ 06 ቀበሌ ነዋሪ ሲሆኑ የግራንት ፈንድ የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ ናቸዉ፡፡ ሰባት ቤተሰብ ያስተዳድራሉ፣ በአራት ቤተሰብ ከሴፍቲኔት ፕሮግራም ድጋፍ ይወስዳሉ፡፡

ባገኙት የ16 ሺህ 3 መቶ ብር ድጋፍ ከግብርና ዉጭ ገቢ ማስገኛ ዘዴ በመሰማራት ሻይ ቤት ከፍተዉ እየሰሩ ይገኛል፡፡

ከሻይ ቤት ስራዉ ጎን ለጎን ሶስት ፍዬሎችን ገዝተዉ እያረቡ በአሁኑ ሰዓት አምስት አድረሰዉ እያረቡ ተጨማሪ ገቢ በማግኘት ላይ ይገኛሉ፡፡

PSNP
Productive Safety Net Programme

አቶ እንድሪስ አሁን ላይ ከምንም ተነስተዉ አሁን ላይ ባለ 30 ቅጠል ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት ሰርተዋል፣ 5 ፍየሎች፣ ከ30 ሽህ ብር በላይ አላቸዉ፡፡ በአካባቢ ያለ አነስተኛ ወንዝን በመጠቀም አትክልትና ፍራፍሬ ያለማሉ፡፡




አቶ እንድሪስ ወደ ፊት ሱቅ ከፍተዉ መስራት ዕቅድ አላቸዉ፡፡ ከተረጅነት ለመዉጣትና ጥሪት ለመገንባት ጠንክረዉ እየሰሩ ነዉ፡፡ በኑሯቸዉም በተጨባጭ መሻሻል እያሳዩ ይገኛል፡፡







ወ/ሮ አሚናት የግራንት ፈንድ ተጠቃሚ ስትሆን አምስት ቤተሰብ አስተዳዳሪ ናት፡፡

ወደ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ከመታቀፏ በፊት ምንም ሃብት ያልነበራት ቤተሰቧን የምታስተዳድር የቀን ስራ እየሰራች ነበር፡፡

በፕሮግራሙ በተሰጣት ነጻ ትራንስፈር በፍየል እርባታ ተሰማርታ ኑሮዋን እየደጎመች ትገኛለች፡፡

PSNP
Productive Safety Net Programme

በኑሮ መሰረት ማሻሻያ ዘርፍ በተደረገላት የ16ሺህ 3 መቶ ብር ድጋፍ ሶስት ፍየሎችን ገዝታ እያረባች ትገኛለች፡፡

ወ/ሮ አሚናት ቤተሰቧን በአግባቡ እያስተዳደረች ትገኛለች፡፡ አሁን ላይ ስምንት ፍዬሎች አሏት፡፡



የወ/ሮ አሚናት ፍዬሎች

## ችግር ያልበገራት፣ ሰርቶ መለወጥ እንደሚቻል ያሳየችው ብርቱዋና ባለ ራዕይዋ ጠንካራ ሴት



ወ/ሮ ክድጃ እንድሪስ

በባቲ ወረዳ ማመድ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ ክድጃ እንድሪስ ወደ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የገባችዉ በ2014 ሲሆን በ4 ቤተሰብ ትደገፋለች፡፡ ወ/ሮ ክድጃ በቤተሰብ የኑሮ መሰረት ማሻሻያ ፕሮግራም በሚሰጥ ብድር የተለወጠችና ሃብት ያፈራች ታታሪ ሴት ናት፡፡

በፕሮግራሙ የሚሰጥ የ40 ሺህ ብር ብድር ወስዳ አንድ በሬ በመግዛትና በማድለብ በሶስት ወር ዉስጥ 60 ሺህ ብር በመሸጥ 20 ሺህ ብር ትርፍ ማግኘት ጀመረች፡፡

ብርቱዋ ሴት ደግማ በ40 ሺህ ብር በሬ በመግዛት አሁንም 60 ሺህ ብር በመሸጥ ድጋሜ 20 ሺህ ብር ትርፍ አገኘች፡፡




አሁን ላይ ወ/ሮ ክድጃ ብድሯን ሙሉ ለሙሉ መልሳ በ36 ሺህ ብር የተገዛች ሁለት ጥጃ የሰጠች ላም አለቻት፡፡

ሰላሳ ዶሮዎችን በ20ሺህ ብር በመግዛት በማርባት ላይ ናት፡፡ በ15 ሺህ ብር የተገዛ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሆን ዉሃ ማመላለሻ የሚሆን አንድ አህያ አላት፡፡




ብድርን በዉጤታማነት የሰራችበት ጀግናዋ ወ/ሮ ክድጃ ሶስት ልጆቿን ታስተምራለች፣ በባንክ ቁጠባ ጀምራለች፡፡ በብዙ ፈተናዎች ዉስጥ አልፌ ከዚህ ደርሻለሁ፣ ሴፍቲኔት ኑሮዬን ለዉጦልኛል ትላለች፡፡

# የአካል ጉዳት ያልበገረዉ

# ሀሰን ሙሀመድ




አቶ ሀሰን አካል ጉዳተኛ ሲሆኑ ወደ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የገቡት በ2008 ሲሆን አምስት ቤተሰብ አላቸዉ፡፡ የአካል ጉዳት ያልበገራቸዉ ታታሪዉ አቶ ሀሰን በብድር መለወጥና ሀብት መፍጠር እንደሚቻል ለአካባቢዉ ማህበረሰብ ያስተማሩ ናቸዉ፡፡

አቶ ሀሰን በፕሮግራሙ በተመቻቸ ብድር 40 ሺህ ወስደዉ በንግድ ላይ የተሰማሩ ሲሆን በጣም ዉጤታማ አድርጓቸዋል፡፡ በመጀመሪያ ሁለት ወይፈኖችን ገዝተዉ በአንድ ወር ዉስጥ 23 ሺህ ብር አገኙ፡፡



ከዚያ በኋላ ደግመዉ ደጋግመዉ እየገዙ፣ እየሸጡና እየለዋወጡ ዉጤታማ የሆኑ የሴፍቲኔት ተጠቃሚ ናቸዉ፡፡ ቤተሰባቸዉን በአግባቡ እያስተዳደሩ ይገኛሉ፡፡

አቶ ሀሰን ብድሩን ከወሰዱት 3ኛ ዓመት ላይ የሚገኙ ሲሆን የሁለት ዓመቱን ከፍለዉ አሁን ላይ የቀራቸዉ የአንድ ዓመቱ ብቻ ነዉ፡፡


አሁን ላይ አቶ ሀሰን አንድ በሬ፣ አንድ ላም፣ አንድ ወይፈን አላቸዉ፡፡ በጥሬ ገንዘብ ወደ 20 ሺህ ብር አካባቢ አላቸዉ፣ በጸደይ ባንክም ይቆጥባሉ፣ ልጆቻቸዉንም የሚያስፈልጋቸዉን እያሟሉ እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡

**በኤዶ መድኔ ተፋሰስ- የሴፍቲኔት**

# ፕሮግራም አበርክቶ



በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን አርጡማ ፉርሲ ወረዳ በኤዶ መድኔ ቀበሌ 2014 እና በ2016 ዓ/ም በገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ካፒታል በጀት የተሰሩ ሁለት የመስኖ ካናሎች ይገኛሉ።





በእነዚህ የመስኖ ፕሮጀክቶች የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች እና ከፕሮግራሙ ዉጭ የሆኑ የአካባቢዉ አርሶ አደሮች በመስኖ ልማት በመሰማራት በዓመት ሁለትና ሶስት ጊዜ በማምረት ተጠቃሚ እየሆኑ ነዉ።

በተፋሰሱ ከ202 ሄክታር መሬት በላይ እየለማ ይገኛል። በዚህም ከ180 በላይ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል።




የተፋሰሱ ተጠቃሚዎች ጤፍ፣በቆሎ፣ ማሾ፣ ማሽላ፣ ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ቃሪያ፣ ጥቅል ጎመን፣ ሙዝ፣ማንጎ…በዓመት

ከሁለት ጊዜ በላይ በማምረት ከተረጅነት ለመላቀቅ ጠንክረዉ እየሰሩ ነዉ።



የሴፍቲኔት ፕሮግራም አበርክቶ

# አሸዋ ሉጤ ቱሉ ካናል ግንባታ



በ2017 በጀት ዓመት በሴፍቲኔት ካፒታል በጀት ከሚገነቡ የመስኖ ፕሮጀክቶች ዉስጥ የአሸዋ ሉጤ ቱሉ ካናል አንዱ ነዉ። ፕሮጀክቱ የሚገኘዉ በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ዉስጥ ነዉ።



አሸዋ ሉጤ ቱሉ ካናል

ግንባታዉ በ4.7 ሚሊዮን ብር በፕሮግራሙ በጀት የተሰራ ሲሆን 530 ሜትር ርዝመት አለዉ። ከ50 በላይ ሄክታር መሬት ያለማል ተብሎ ይጠበቃል።

ከ1 መቶ በላይ የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችንና ከፕሮግራሙ ዉጭ የሆኑ የአካባቢዉ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል።




## ዲምቱ የመስኖ ካናል ቀበሌ



1 ሺህ ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለዉ ዲምቱ የመስኖ ካናል በ2017 በጀት ዓመት በፕሮግራሙ ካፒታል በጀት እየተገነባ ነዉ። ዲምቱ

PSNP
Productive Safety Net Programme

የመስኖ ካናል የሚገኘዉ በአርጡማ ፉርሲ ወረዳ ዲምቱ ቀበሌ ዉስጥ ነዉ፡፡



ዲምቱ የመስኖ ካናል

2 መቶ 27 ሄክታር መሬት በመስኖ ያለማል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ፕሮጀክቱ ከ200 በላይ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ያደርጋል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን ከእነዚህ ዉስጥ ወደ 58 የሚሆኑት የሴፍቲኔት ተጠቃሚ የሆኑ አርሶ አደሮች ናቸዉ፡፡



በዲምቱ የመስኖ ካናል እየለማ ያለ የመስኖ ልማት

# "ኮልባ" የማህበረሰብ ኩሬ



"ኮልባ" የማህበረሰብ ኩሬ የሚገኘው በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ደዋ ጨፋ ወረዳ ሽክላ ቀበሌ ነው፡፡ ኩሬው በጥልቀት የተቆፈረ ሲሆን 10*10 የሆነ ስፋት አለው፡፡

ወደ ተፋሰሱ 1 ሽህ ሜትር ርዝመት ባላቸው ኤች ዲ ፒ ቱቦዎች ወደ ጊዜያዊ የውሃ ማጠራቀሚያ ሮቶዎች እና ጆኦ-መብሬን እንዲገባ ይደረጋል፡፡ 3 ሽህ ሜትር ርዝመት ባላቸው ቱቦዎች ደግሞ በስበት ሃይል ወደ ልማቱ እንዲገባ ተደርጎ ጥቅም እየሰጠ ይገኛል፡፡



በኩልባ የማህበረሰብ ኩሬ እየለማ ያለ

PSNP Productive Safety Net Programme

የማህበረሰብ ኩሬው በቀበሌው ለሚገኙ የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችና ለአካባቢው አርሶ አደሮች ለመስኖ ልማት እና ለኮልባ ተፋሰስ ልማት ቋሚ የውሃ አማራጭ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

ከ10 ሄክታር በላይ መሬት በሰብል፣ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት እያለማ ሲሆን በዚህም 49 አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ እያደረገ ነዉ። ከእነዚህ ውስጥ ከ10 በላይ የሚሆኑት የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ናቸዉ።




በሸክላ ቀበሌ የሚገኙ የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች በኮልባ ተፋሰስ በማህበር ተደራጅተው የተለያዩ ማንጎ፣ ቡና፣ ሎሚ፣ ግራቭሊያ (ለጣውላ የሚሆን) እና ሌሎችን እያለሙ ተጠቃሚ እየሆኑ ነው።

ሌላው የማህበረሰብ ኩሬው በአካባቢው የእርሻ መሬት ያላቸው ተጠቃሚዎች/ አርሶ አደሮች በመስኖ ልማት ማለትም ሽንኩርት፣ በቆሎ፣ ጥቅል ጎመን፣ ቲማቲም፣ ቃሪያ እና ሌሎች አትክልትና ፍራፍሬዎችን በማልማት የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ እየተጉ ይገኛል።



የውሃ ማቆርን ከተፋሰስ ልማትና ከመስኖ ስራ ጋር በማስተሳሰር ጥሪት እንዲገነቡ በትኩረት እየተሰራ ነዉ፡፡

የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች በሚደረግላቸው ድጋፍ የኩሬ ውሃውን በመጠቀም በአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም በሰብል ልማት ተሰማርተው በምግብ ራሳቸውን እንዲችሉና ከተረጅነት እንዲላቀቁ ለማስቻል ታልሞ የተሰራ ነው፡፡




# የተፋሰስ ልማቱ ተጠቃሚ

በኮልባ የማህበረሰብ ኩሬና በተፋሰሱ እየተጠቀሙ ያገኘናቸው የሴፍቲኔት ተጠቃሚ አቶ አደም ባቦ ሮቦ ይባላሉ፡፡ የሚኖሩት በሸክላ ቀበሌ ሲሆን ሰባት ቤተሰብ አላቸው፡፡ በማህበረሰብ ልማት ስራ በአምስት ቤተሰብ ከፕሮግራሙ ለ6 ወራት ድጋፍ ያገኛሉ፡፡




40 ሽህ ብር የሚያወጣ ሞተር ፓምፕ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህም የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎችን በተፋሰሱ ውስጥ እያለሙ ይገኛል፡፡

የግራንት ፈንድ ተጠቃሚ እንዲሆኑና ተጨማሪ ሃብት አፍርተው ከፕሮግራሙ እንዲመረቁ ለማስቻል አዋጭና ተስማሚ በሆነና በመረጡት ዘርፍ ተሰማርተዉ ራሳቸዉን ችለዉ ከፕሮግራሙ ለመዉጣት ጠንክረዉ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

# ከ20 በላይ ወጣቶችን ተጠቃሚ ያደረገዉ "ማንገዶ" የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት



"ማንገዶ" የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት የሚገኘው በአማራ ክልል ኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ደዋ ሃረዋ ወረዳ "ካሪጾ" ቀበሌ ሲሆን ከ20 በላይ ወጣቶች ተደራጅተው ገቢ በሚያስገኙ ፍራፍሬዎችና በደን ልማት ተጠቃሚ እያደረገ ነው።

ማንገዶ የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት ከ2.5 ሄክታር በላይ ስፋት አለዉ።




በሴፍቲኔት ፕሮግራም ውስጥና ከሴፍቲኔት ውጭ ያሉ የአካባቢው ወጣቶች ቋሚ ፍራፍሬዎችን ማለትም የፓፓያ፣ የማንጎ እና የደን ልማቶችን በማልማት ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ።

# ሀረዋ የመስኖ ፕሮጀክት



በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን በደዌ ሃረዋ ወረዳ ሀረዋ ቀበሌ ዉስጥ ሀረዋ ዶቤ የመስኖ ፕሮጀክት በሴፍቲኔት ካፒታል በጀት በ2017 በጀት ዓመት ግንባታ ተከናዉኗል።




የመስኖ ፕሮጀክቱ ዊር እና 700 ሜትር ርዝመት ያለው ካናል ሲሆን በገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ካፒታል በጀት ከ5

PSNP
Productive Safety Net Programme

ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ በጀት ተገንብቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

የመስኖ ካናሉ በሁለት አቅጣጫ እየተገነባ ሲሆን ከ35 ሄክታር በላይ የሚያለማ ሲሆን ከ80 በላይ አርሶ አደሮችን ደግሞ በመስኖ ልማት ተጠቃሚ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል።




ከእነዚህ ዉስጥ ከ40 በላይ የሚሆኑት ተጠቃሚ አርሶ አደሮች የሴፍቲኔት ተጠቃሚ የሆኑ አርሶ አደሮች ናቸው።



# ከ11 በላይ ወጣቶችን ተጠቃሚ "ጎቦ" የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት



"ጎቦ" የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት በደዌ ሃረዋ ወረዳ በሃረዋ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የለማው በገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የማህበረሰብ ልማት ዘርፍ ነው።

በሴፍቲኔት ፕሮግራም የታቀፉ ከ11 በላይ ወጣቶችን ተጠቃሚ እያደረገ ነው። ገቢ በሚያስገኙ የተለያዩ ፍራፍሬዎችና ደን ልማት ጋር በተቀናጀ መልኩ እየተሰራበት ነው።

PSNP Productive Safety Net Programme

ተፋሰሱ አጠቃላይ 520 ሄክታር ስፋት ሲኖረው የፊዚካል ስራ የተሰራበትና የለማው ግን 30 ሄክታር የሚሆነው ነዉ፡፡

የውሃ ቧንቧዎች ዝርጋታና የፍራፍሬዎች ችግኝ ለተጠቃሚዎች ተገዝተው የቀረቡት በፕሮግራሙ የካፒታል በጀት ነው፡፡



የተፋሰስ ልማቱ ተጠቃሚ



"ጎቦ" የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት

በተፋሰሱ በተሰሩ የጠረጴዛ እርከኖች ላይ ማንጎ፣ ስኳር ድንች፣ ለውዝ፣ አኩሪ አተር እንዲሁም በቆሎ እያመረቱ እየተጠቀሙ ይገኛል፡፡ ገቢያቸውንም በማሳደግ ላይ ይገኛሉ፡፡